በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 218822
ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ መሃሪ አለምሶም-ጠበቃ ፈቃደ ተፈራ- ቀረቡ

ተጠሪ፡- የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤሕግ-አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍርድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 693(1)ን በመተላለፍ በቀን 20/03/2013 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:30 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በሀዋሳ ከተማ መሃል ክፍለ ከተማ ንጋት ኮከብ ሆቴል ውስጥ ልዩ ቦታው አረብ ሰፈር በሚባልበት ከግል ተበዳይ ሉቻ ተክሉ የምትነግድበት ሥራ ቦታ ድረስ በመሄድ በኦሮሚያ ክልል እና ሲዳማ ክልል የቢሮ ዕቃዎች ለማስገባት ጨረታውን ስላሸነፍኩ ብር ቸግሮኛል በጋራ እንሰራለን ብር አበድሪኝ በማለት በተለያየ ቀን ዕቃዎችን ለመግዛት ብሎ በካሽ እና በአካውንት የወሰደውን ብር በንግድ ባንክ በሁለት ግዜ እንዲከፈል ሲል ቼክ ቁጥር BC19664274 በሆነው 1,600,000 (አንድ ሚሎዮን ስድስት መቶ ሺህ ብር) ቀን 30/3/2013 ዓ.ም ጽፎ የሰጠ በመሆኑ እንዲሁም በቼክ ቁጥር BC19664275 በሆነው 1,500,000

(አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) በቀን 15/4/2013 ዓ.ም ጽፎ በመስጠት በአጠቃላይ ብር 3,100000 (ሶስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ብር) የሚሆን በአመልካች ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ እንደሌለ አጣርቶ መረጃ የተሰጠ በመሆኑ በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክ በማዘዙ ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ የሌለው መሆኑን፣ የእምነት ክህደት ቃሉ ሲጠየቅም የወንጀሉን ድርጊት አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤትም ተጠሪ ክስ የቀረበበትን የወንጀል ድርጊት ስለመፈጸሙ በዓቃቤሕግ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል በሚል በተከሰሰበት የወንጀል ህግ ቁጥር 693(1) ስር እንዲከላከል በማለት ብይን ተሰጥቷል፡፡

አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 142/3 መሠረት ቃሉን ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ አመልካች በንግድ ባንክ በሁለቱም ቼክ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ እንደሌለ ተረጋግጧል፤ አመልካች ቼኩን መስጠቱን አልካደም፤ አመልካች በዓቃቤሕግ የተረጋገጠበትን ፍሬነገሮች አልተከላከለም በማለት በወንጀል ህግ ቁጥር 693(1) ስር ጥፋተኛ ብሎ አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብለት ያቀረበው ማስረጃ ተገቢነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎ በ4 ዓመት ጽኑ እስራት እና በ2000 (ሁለት ሺህ ብር) እንዲቀጣ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት የተጣለበትን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ እንዲታረምለት በክልሉ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ቢያቀርብም ውሣኔው ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

አመልካች ታህሳስ 7 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡- የወንጀሉን ድርጊት ለመፈጸም የሀሳብ ክፍል እንደሌለኝ ተረጋግጧል፤ አመልካች ከክሱ በፊት የተገለጸውን ገንዘብ ስለመክፈሌ የባንክ ሰነድ በማቅረብ አረጋግጫለሁ፤ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብልኝ ያቀረቡትኩትን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ.ቁ. 122766 እና 171403 እና 177216 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ ውሣኔ የሚቃረን ነው፤ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በገደብ ለመለቀቅ ያቀረቡትን አቤቱታ ስር ፍርድ ቤት በማለፍ የወሰነበትን አግባብነት ከወንጀል ህግ ቁጥር 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አንጻር ለማጣራት በሚል ማስቀረቢያ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ አቤቱታው ከመጥሪያ ጋር ደርሶት መጋቢት 20 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጠው መልስ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 197 ላይ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች እንዳሟላ አልተረጋገጠም፤ አመልካች ብር 2,300,000 (ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሺ ብር) አልከፈለም፤ በክስ ሂደትም መክፈሉን አላስረዳም፤

*አመልካች በሰበር ቅሬታው ላይ የጠቀሳቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠባቸው መዝገቦች ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የላቸውም፤ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገብ ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚህ ተጠናቋል፡፡*

*የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ በስር ፍ/ቤት ከተጠረገው አጠላይ ክርክር እና ከተሰጡ ውሣኔዎች እንዲሁም ከማስረቀርቢያ ነጥቡ አንፃር ከጉዳዩ ጋር አርባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማረናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡*

*እንደመረመርነውም አመልካች በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ ሰጥቷል በሚል የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ ስር ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት የተወሰነበት መሆኑን እና ይህ ውሣኔም በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች መጽናቱን ተመልክተናል፡፡ ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ አመልካች ቅጣት እንዲገደብለት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ሊያጣ የቻለው በህግ አግባብ ስለመሆን አለመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡*

*በአንድ የወንጀል ጥፋተኛ ላይ የተወሰነው ቅጣት አፈፃፀሙ ለተወሰነ የፈተና ጊዜ ተገድቦ ስለሚቆይበት ሁኔታ ወይም መስፈርቶችን በሚመለከት፡-*

*ጥፋተኛ የተባለው ሰው አስቀድሞ የተፈረደበት መሆን አለመሆኑ ግምት ውስጥ ሣይገባ፣ቅጣቱ ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ታግዶ ቢቆይ አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ የጥፋት ድርጊት ከመፈፀም የሚቆጠብ ወይም የሚታገድ ስለመሆኑ ሲታመንበት እና ፣ ስለአመሉ መሻሻል አንድ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃው መሆንኑ ፍ/ቤቱ ሲያምንበት የተወሰነው ቅጣት አፈፃፀም በገደብ ሆኖ እንዲቆይ ሊወስን እንደሚችል የወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 ይደነግጋል፡፡*

*ከዚህ በተጨማሪም በጥፋተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይፈፅም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 197 ላይ የተደነገጉት ማለትም በመልካም ጠባይ እንደሚመራ የተጣለበትን የገደብ ግዴታ የሚቀበል በተቻለው መጠን በጥፋቱ ምክንያት ያደረሰውን ጉዳት ሁሉ እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍል እንዲሁም የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ሲሰጥ እንደሆነ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 197 ይደነግጋል፡፡*

*እንዲሁም የወንጀል ህግ አንቀጽ 195 እና 196 ድንጋጌዎች የሚያዩት የቅጣት ገደብ ጥያቄ ጥፋተኛ በተባለው ሰው ስለተጠየቀ ብቻ የሚሰጥ መብት ሳይሆን የዳኞችን ፍቅድ ሥልጣን መሠረት ያደረገ እና የሚከለከልም ሆነ የሚፈቀድ ሲሆን ክርክር የሚደረግበትና ማስረጃም የሚቀርብበት ስለመሆኑ ህጉ በግልጽ ደንግጓል፡፡*

*ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ቅጣት እንዲገደብለት ያቀረበው ምክንያት የደም ግፊት ህመምተኛ መሆኑ እና ይህን ለማስረዳትም የህክምና ማስረጃ እንዳቀረበ በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ የስር*

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ፍ/ቤት አመልካች ቅጣት እንዲገደብለት ያቀረበው ምክንያት በህክምና ማስረጃ ስለመደገፍ አለመደገፉ ሲገልጽም ማስረጃው እረፍት ያድርግ የሚል እንጂ የህመሙን አደገኛነት አይገልጽም የሚል ነው፡፡

የቀረበውን የገደብ ምክንያት አስመልክቶ ፍ/ቤቶች በህግ አግባብ ሊመረምሩ የሚገባው በመሆኑ የምክንያቱን በቂና አሳማኝነት እንዲሁም በህጉ ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ የመሆኑን አግባብነት ጭምር ሊመረምሩ ይገባል በተመሳሳይ ጉዳይም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 223884 በቅርቡ ትርጉም የተሰጠበት መሆኑንም መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም አመልካች ቅጣት እንዲገደብለት ያቀረበው ምክንያት የደም ግፊት በሽተኛ መሆኑ እና ሀኪም እረፍት እንዲያደርግ የሰጠውን ማስረጃ ሲሆን ይህ አመልካች ያቀረበው ምክንያት በስር ፍ/ቤት ከአጠቃላይ ሁኔታው የጥፋተኛውን የቀድሞ ታሪኩ፣ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ በችሎቱ የተረጋገጡትን እውነታዎች መነሻ በማድረግ ለመመዘን የሚያስችሉ አሳማኝ እና በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ታግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች አይደሉም ሲል ቅጣቱ እንዲፈፀም የደረሰበት መደምደሚያ ህግን እና አመልካች ያቀረበውን ማስረጃ መሠረት ያደረገ እንጂ የሚነቀፍ እና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የማያስደፍር በመሆኑ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 02116 በ17/03/2014 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/01482 በ11/02/2014 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 30430 በ30/10/2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ቅጣት ውሣኔ እና በ24/10/2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 192/2/ለ/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

- የዚህ ውሣኔ ትክክል ግልባጭ አመልካች ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት እና ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

**መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘርቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም